# ብረቱካን - የወ/ሮ አልማዝ ልጅ፣ የሃሌ እናት ብቻ!?

የአንድነት ከፍተኛ የአመራር አባል አቶ ሰዬ አብርሃ በቅርቡ እንዳሉት „ብረቱካን ወታጥ ነች ይቅርታ ይደረግላትና ከስር ተፈታ፣ ልጁዋን ታሳድግ፣ አሮጊት እናቷን ትጡር" ሲሉ ወንድማቸውን አቶ መለስ ዜናዊን ተማጥነዋል። አዎ ብርቱካን አንድ ህጻን ልጅ፣ ከሰባ ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው አሮጊት አናት ያሏት፣ በእርግጥም በ30ዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የምትገኝ፣ ወጣት ነች። አቶ ሰዬ „ህጻን ልጇን ማሳደግ፣ አሮጊት እናቷን መርዳት እንድትችል ይቅርታ ይደረግላት" ማለታቸውን የሰሙ እናቶችና አባቶች ሆዳቸው ምን ያህል እንደሚንቦጫቦጭ መገመት የሚያስቸግር አይደለም። እናትም አባትም ያልሆኑ ወጣቶችም አዝነው እንባቸው ሲፈስ ተመልክቻለሁ። እኔም በወለደ አንጀት ባይሆንም አዝኛለሁ።

ይቺን ጽሁፍ ለመጫር የተነሳሁት ግን ከዚህ በላይ ባቀረብኩት ሃሳብ ተመስርቼ ሳይሆን፣ ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ በሌላ ቦታና በሌላ ጊዜ ባጋጠመኝ ክስተት መነሻነት ነው።

እንዲህ ነው ጉዳዩ፣ ዕለቱ ባአንድ የልደት በአሉን በሚያከብር ሰው ቤት ወደ 8 የምንሆን ሰዎች ተሰብስበናል። ጨዋታ ደርቷል የባጥ የቆጡ ይነሳል ይጣላል። የጨዋ ልጅ መጫወቻዎችም በያይነቱ ተደርድረዋል። መሃላችን ስለ ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ ጆሯቸውን ቢቆርጧቸውም ምንም ከማይሰሙና ከማይለሙ ጀምሮ፣ ከጧት እሰከማታ ከኢትዮጵጵያ የፖለቲካ ውዝግብ እስከማይለዩ ድረስ የተደባለቅን ነን። ታዲያ በዚህ መሃል ነበር አንዱ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ አድናቂ „ታውቀላችሁ? በዚህ ሰሞን በጣም ያናደደኝ ነገር፣„ ይልና እራሱን መደባበስ ያዘ። አንዱ ከመሃላችን „ምን ሆንክ ደግሞ? እንግዲህ አንተ መቼም ትንሽ ስትወራውር ትንቢተኛ ነኝ ማለት ይቃጣሃል።" ሲለው „አንተ ትቅልዳለህ ሳትሰማ ቀርተህ ነው? ያቺን ጀግና ሴት እኮ ልጇን እንድታሳድግና እናቷን እንድትጦር ከስር ትፈታ ሲል ፓርቲዋ ጠየቀ፣ አያናድድም? ይልና ዘራፍ ይላል፣ አንዲት ሴት ነገሩ ስላልገባቸው እጎናቸው ያለውን ሰው ቀስ ብለው „ምኑ ነች እህቱ ነች? ሲሉ የጠይቃሉ፣" የዚህ ጊዜ አስተናጋጃችን የፖለቲካ ጉዳይ ከተነሳ ትርምስ ይፈጠራል ብሎ በመፍራት፣ የባለቤትነት መብቱን ተጠቅሞ፣ እንግዲህ ይሄንን ፓርቲ ምናምን የምትሉትን ጣጣ ተዉ፣ በዓል እናክብር አለና ሙዚቃውን ከፍ አደረገው።

ለጊዜው ሁላችንም ጭጭ አልን ሙዚቃው መጮሁ ብቻ ሳይሆን ተወዝወዙ የሚልም ጭምር ስለነበር፣ ግማሹ ተነስቶ ትከሻውን ሲያሳይ ሌላውም በተቀመጠበጥ መናጡን ተያያዘው፣ እኔም ያ የብርቱካን አድናቂ ያነሳው ጉዳይ ከነከነኝና ቦታዬን ቀይሬ አጠገቡ ጠጋ ብዬ ሃሳቡ ባለምደመጡ ቅር ብሎት እንዳይደበር አይዞህ በማለት ላረጋጋው ስሞክር፣ „እባክህን ተወኝ! ሲጋራ ላጭስ ወጣ ብዬ" - እቤት ውስጥ ስለማይጨስ- ሲለኝ፣ ጥሩ እኔም ንፋስ እቀበላለሁ አልኩና አብሬው ወጣሁ። እንዳጋጣሚም ከመሃላችን ሲጃራ የሚያጨስ እሱ ብቻ ነበር። ወዲያው እደጅ እንደወጣን ሲጋራውን አቀጣጠለና ምንም ሳይዘገይ፣ „ታውቃለህ? መለሰ ዜናዊ ዋሺ ሲላት እኮ ደፍራ አሻፈረኝ ያለች ጅግና ነች። ሰላማዊ ትግል ማለት ይሄ ነው። የማይሆን ነገር አድርጉ ሲባል እምቢታኛነትን ማሳየት እኮ ነው። ብርቱካንን በቴሌቪዥን ካልሆነ በስተቀር በአካል አይቻት አላውቅም። ቃሌ የሚለውን ጽሁፏን አንብበኸዋል? ያ ጽሁፏ የመጨረሻ እንደሚሆን ሁሉ የተናገረችውን? እንደምትታሰር ታውቀው ነበር ማለት እኮ ነው። ብትፈልግ እኮ ልትጠፋ ትችል ነበር። እንደሚባለውማ እውጭ አገር እንድትቀር ሁሉ ይፈለግ ነበር ነው የሚባለው። እኔን እኮ አሁን በጣም ያናደደኝ ብርቱካን ለኢትየለጵያ አንድነት፣ ለሕዝብ ነጻነትና ለፍትህ ስትል እንጂ፣ እንደምትታሰር እያወቀች እያለ የምታሳድጋት ልጅ፣ የምትጠራጥ እናት እንዳላት ሳታውቅ ወይም ረስታ ነው ያደረገችው ብሎ ፓረቲዋ ሊያሳምነን መሞከሩ አሳፋሪ ተግባር ሆኖ ነው የማየው። እስቲ ፍረድ" ሲል አፋጠጠኝ።

ትንሽ ካሰብኩ በሁዋላ፣ እርግጥ ልጇን ጥሩ ት/ቤት አስገብታ በማስተማር ደህና ስራ እንድታገኝ፣ ወደፊትም ጎጆ ስትወጣ የሚሆናት ቤትም ሰርታላት፣ እናቷንም ቢሆን ስላረጁ ሰራተኛ ቀጥራላቸው ብትጠራቸው ጥሩ ነበር። ብዙ እንደሷ የተማሩ ሰዎች የሚያደረጉት እንደዚህ ነው። አልኩት። የዚህ ጊዜ ወንድሜ አይኑን አፍጥጦ „እና መዋሸት ነበረባት ማለት ነው? ደግሞ ለልጇ ቤት ሰርታ ምናምን የምትለው ብርቱካን ለልጇ ብቻ ሳይሆን ላጠቃላዩ የነገ ትውልድ ነጻነትን ለማውረስ የተነሳች መሆኗን አልተገነዘብክምና ነው!?" አለና ጮኸብኝ። አሁን እኔም ትንሽ ደፈር ባለ ድምጽ ይሄ መንግስት እኮ ዕውነትና ውሸት አይለይም እሱ በሽማግሌ አልተፈታሽም ብሎ ሁለት ጠጉር ያወጣውን ሽማግሌ፣ የእግዚአብሕርን ቃል የያዘ ነው የሚባለውን መጽሃፍ ቅዱስ ገላጩን ቄስና በዓለም የታወቀውን ላብ-አደር ሽምጋዮች በዚህ ዓለም እንደሌሉ አድርጎ አሽቀንጥሮ አንጦሮንጦስ ጥሎ ሲዋሽ፣ እሷም በተቀደደው ቀዳዳ ዘው ብላ ገብታ እነዚህን አጭበርባሪዎቹን በህግ እፋርዳለሁ ለክ ነገሩ እርስዎ እንዳሉት ነው ብላ ብትሸውደው ምን ነበር ችገሩ? አልኩት። „እስቲ ድገምልኝ ሃሳብህን በደምብ አልያዝኩትም" አለኝ። ደገምኩለት። አልተቀበለውም ለህሊናዋ የሚስማማት አይደለም አለና „ይልቅስ አሁን ፓርቲው ልጇን እንድታሳድግ እናቷን እንድትጦር ይቅርታ ይደረገላት ወደሚለው ጉዳይ እንመለስ አለኝ።" እሱማ መቼም በሰብአዊ ርህራሄ መልክ ከታሰበ ክፋት ያለው አይመስለኝም ስለው፣

ያለ ይመስለኛል። ለዚህም አሁን ወያኔው በፓርቲሽም በኩል ቅድሚያ የተሰጠው ያንች ከስር ወጥተሽ የግል ህይወትሽን መምራት እንድትችይ ስለሆነ፤ ሁለተኛ ወደፖለቲካው ሜዳ የምታደርጊውን መቅለብለብ ከተውሽ እፈታሻላሁ ቢላት ምንድነው የሚባለው እስቲ ሃሳብ ስጥ“ አለኝ።

ድንግጥ አልኩ፤ እኔ በሃልዮም፤ በነቢርም፤ በገቢርም ያላሰብኩት ጉዳይ ስለሆነ፤ ወዲያውን መልስ ለመስጠት አልሳካ አለኝ። ያልሆነ መልስ እንዳልሰጥ ብዬም አንዳንዴ ሰው የሚሄድበት መንገድ ስለማይታወቅ መጠንቀቅ ያስፈልጋል አልኩና እስቲ ወደቤት እንግባና ትንሽ ደግሞ ሙዚቃም፤ ምናምንም እንበል፤ አስቤ ሃሳቤን እሰጥሃለሁ አልኩና ወደቤት ገባን።

እኔ ለስሙ ወደቤት ገባሁ እንጂ፤ ከሙዚቀውም ከምኑም  ነገር ተሳታፊ አልነበርኩም። ሳውጠነጥን የቆየሁት ለቀረበልኝ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነበርና የማውጣት ማውረድ ሙከራዬ በመሰረቱ የአንድነት አመራር ያንን ተማጥኖ ለእቶ መለስ ሲያቀርብ ከላይ ተከራካሪዬ የደረሰበትን ጥርጣሬ እንዴት ሊያስከትል እንደሚችል እራሴን ለማሳመን የሚያስችለኝን የግል መመዘኛ ለማግኘት ስለነበር ብዙ ጊዜ ፈጀብኝ። እኔ በዚህ ላይ እንዳለሁ፤ ያ ተከራካሪዬ እንደገና ሲጃራ ለማጨስ ወደውጭ ወጣ። እኔም አብሬው ወጥቼ መልስ እንደምሰጠው አስቦ ስለነበር እውጭ ሆኖ በመስኮት እያየኝ፤ እጁን እያውለበለበ ምነው ብቅ አትልም እንዴ የሚል ምልክት ያሰየን ነበር። እኔም ገና እንዳልተዘጋጀሁ አይነት የሚያሳይ ምልክት በማሳየት አቀርቅሬ ማውጣት ማውረዴን ቀጠልኩ።

በመጨረሻም አንድ ነገር ትዝ አለኝ። የቅንጅት አመራሮች ሲፈቱ ብዙ ወር የተለፋበት የሽምግልና ውጤት ነው የተባለው ያለጠፉትን አጥፍተዋል ተብሎ በተቀናጀ ዘዴ ነው የተፈቱት፤  ስለዚህ ብርቱካንንም ከፓርቲዋ በተጠየቀው መሰረት ለልጇና ለናቷ ስትል ይቅርታ ጠይቃ ተፈታለች በሚያሰኝ መልክ ለመፍታት መንገድ መቀየስ የሚያዳግት መስሎ ስላልታየኝ የተከራካሪዬን ጥርጣሬ ለመካፈል ተገደድኩ። ጥያቄውን ይዘው ወደ ቃሊቲ የሚሄዱ „ሽማግሌዎች“ ተዘጋጅተው ይሆን?

የታጋይዋ የእስራት ጊዜ እንዲያጥር እየተመኘሁ

አሸብር

kurk1930@yahoo.de